ውሣኔም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የሚባል አይደለም፡፡ ስናጠቃልለው አመልካች ኃላፊነትንና የተቋረጠ ጥቅምን በተመለከተ ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡ በሌላ በኩል በተቋረጠ ጥቅም ስም የተጠየቀውን የገንዘብ መጠን በተመለከተ የተሰጠውን የውሣኔውን ክፍል ማሻሻል እንደሚገባ አምነንበታል፡፡ ስለዚህም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00252 ሚያዝያ 11 ቀን 96 ዓ.ም. እና በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በቁ. 31541 ጥቅምት 2 ቀን 99 ዓ.ም. የተሰጡት ውሣኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽለዋል፡፡
2. አመልካች በተጠሪው መኪና ላይ የደረሰውን ጉዳት የመካስ ኃላፊነት አለበት፡፡ በመሆኑም መኪናውን አስጠግኖ ለተጠሪ የማስረከብ እና የተቋረጠውን ጥቅም የመክፈል ኃላፊነት አለበት ብለን ወስነናል፡፡
3. ተጠሪ በተቋረጠ ጥቅም ወይም ገቢ ስም ሊከፈለው የሚገባ ካሣ በክሱ በግልጽ የጠየቀው ብር 130,400 /አንድ መቶ ሠላሣ ሺህ አራት መቶ ብር/ ነው ብለናል፡፡ አመልካች ይህንኑ ገንዘብ ለተጠሪ ይክፈል፡፡
4. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጡት ውሣኔዎች አልተነኩም፡፡
5. ተጠሪ በመኪናው አለመጠገን በቀጣይ የደረሰበት ኪሣራ ካለ ክስ አቅርቦ የመጠየቅ መብቱ ይህ ውሣኔ አያስቀርበትም፡፡
6. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር የደረሰውን ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
7. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡
8. ከፌ/ከ/ፍ/ቤት የመጣው መዝገብ ቁ. 31541 ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 31334

ሐምሌ 1 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

መድኀን ኪሮስ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - ነ/ፈጅ ኃይሉ ተሰማ

**ተጠሪ፡-** 1/ ወ/ሮ ለተብርሃን በየነ

2/ የአቶ ገብረኪዳን ገዳ ወራሾች እነ ፋሲል ገ/ኪዳን - ጠበቃ ኃ/ማርያም ኢቲቻ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የሰበር አቤታውም ሊቀርብ የቻለው አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረበው ክስ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቶ ተጠሪዎች ባቀረቡት የተከሳሽ ከሣሽነት ክስ መሠረት አመልካች የተጠየቀውን ገንዘብ ሊከፍል ይገባል ተብሎ በመወሰኑ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ አመልካች በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ ባቀረበው ክስ ከሣሽ ንብረትነቱ የአቶ ደረጀ ጉደታ ለሆነ ተሽከርካሪ በደቡብ አብይ ቅርንጫፍ አጠቃላይ የመድን ዋስትና ሰጥቶ በእንቅስቃሴ ላይ እንዳለ ንብረትነቱ በአቶ ገ/ኪዳን ገዳ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ መኪና በመገጨቱና ከፍተኛ ጉዳት መድረሱ ለደረሰው አጠቃላይ ውድመት ከሣሽ ተገቢውን ካሣ የከፈለ ሲሆን በደረሰው አደጋ ጥፋተኛው የተከሣሽን መኪና ሲያሽከረክር የነበረው ግለሰብ እንደሆነ በማስረጃ

ተረጋግጧል፣ ይሄው አደጋውን ያደረሰው ተሽከርካሪ በኢትዮጵያ መድን ድርጅት ሰሜን ምዕራብ ዓቢይ ቅርንጫፍ የመድን ዋስትና ስለነበረው በዚሁ መሠረት በ3ኛ ወገን ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት እስከ ብር 100 ሺህ ካሣ ለመክፈል ከሣሽ ኃላፊነት ስለነበረበት ይህንን ገንዘብ በቀጥታ ጠያቂ ለሆነው ለደቡብ ዓቢይ ቅርንጫፍ እንዲከፍል ተደርጓል፡፡ ስለሆነም የተከሣሽ መኪና በሌላ የ3ኛ ወገን መኪና ላይ ባደረሰው ጉዳት በዋስትና ከተገባው የ3ኛ ወገን ኃላፊነት ጣሪያ በላይ የሆነውን ብር 369,342.00 እንዲከፍሉ ይወስንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

ተከሣሽ አቶ ገብረኪዳን ገዳ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ስለተባለ የሟች ሚስትና ወራሾች በክርክሩ እንዲተኩ ተደርጎ በሰጡት መልስ አደጋ አደረሰ የተባለው የሰ/ቁ. 3-38201 መኪና በከሣሹ የመድን ሽፋን የተሰጠው ስለሆነና ጉዳቱም የደረሰው በሁለቱም መኪናዎች ላይ በመሆኑ በዚሁ መሠረት በሁለቱም መኪናዎች ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሣ መክፈል ስለሚገባው እኛን መጠየቅ አይችልም በማለት የተከራከሩ ሲሆን በሌላ በኩልም የተከሣሾች መኪና በግጭቱ መውደሙ በከሣሽ የታመነ ስለሆነ የመኪናውን የዋጋ ግምት ብር 265 ሺህ የቅሪቱን ዋጋ እና የተቋረጠ ገቢን ጨምሮ በድምሩ ብር 488 ሺህ ከሣሽ እንዲከፍል ይወስንልን በማለት የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አቅርበዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ዋናውን ክስና የተከሣሽ ከሣሽነት ክሱን መርምሮ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ለተጎጂውም ሆነ ለጉዳት አድራሹ መኪና የመድን ሽፋን የሰጠ እንደመሆኑ መጠን ከንግድ ሕግ ቁጥር 663 እና 664 አኳያ ለሁለቱም ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ስላለበት ለተከሣሾች ካሣ የመክፈል ግዴታ አለበት ካለ በኋላ መጠኑን በተመለከተ ከሣሽ ብር 92 ሺህ ካሣ ለመክፈል መስማማቱን ከቀረበው ማስረጃ መረዳት የተቻለ ስለሆነና የመኪናውም ቅሪት ብር 250 ሺ. እንደሆነ ስለተረጋገጠ ይህንን ክፍያ ለመፈጸም ከሣሽ ፈቃደኛ የነበረ ቢሆንም ያልፈጸመ በመሆኑ በድምሩ ብር



342 ሺህ በመኪናው ላይ ለደረሰ ጉዳት ካሣ መክፈል ያለበት ስለሆነ የሟች ሚስት የሆኑት ወ/ሮ ለተብርሃን በየነ ግማሹን ማግኘት ስለሚገባቸው ብር 171 ሺህ እንዲከፈላቸው እንደዚሁም የተቋረጠ ገቢን በተመለከተ ወ/ሮ ለተብርሃን በየነ መኪናው ተጠግኖ ሥራ ቢጀምር ፈቃደኛ መሆናቸውን በ6/2/96 ዓ.ም. ባቀረቡት ማስታወሻ ለከሣሽ ያረጋገጡ ቢሆንም በዚሁ መሠረት መኪናው ተጠግኖ ያልተሰጣቸው ስለሆነ መኪናውን ለመጠገን ያስፈልጋል ተብሎ የሚገመተው የ3 ወር ጊዜ ተቀንሶ ከ6/7/96 እስከ 18/4/98 ዓ.ም. ላለው የ1 ዓመት ከ8 ወር ከ12 ቀናት የተቋረጠ ጥቅም ከሣሽ መክፈል ይገባዋል ካለ በኋላ መጠኑን በተመለከተም ወ/ሮ ለተብርሃን በየነ መኪናው በቀን ብር 700 ገቢ ያስገኝ እንደነበር በመግለጽ በዚሁ ተሰልቶ ካሣ እንዲከፈላቸው የጠየቁትን በመቀበል በዚሁ ስሌት መሠረት የወ/ሮ ለተብርሃን በየነ ድርሻ ብር 214,200 ስለሚሆን ይህንን የተቋረጠ ገቢና ከላይ የተጠቀሰውን የመኪና ጉዳት ካሣ ጨምሮ በድምሩ ብር 385,200.00 ከሣሽ ለወ/ሮ ለተብርሃን በየነ እንዲከፍል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በሌላ በኩልም ከሣሽ ያቀረበውን ክስ በተመለከተም ከሣሽ ለወ/ሮ ለተብርሃንም ሆነ ለአቶ ገ/ኪዳን ገዳ ወራሾች ምንም ዓይነት ክፍያ ሳይፈጽም ክሱን በአቶ ገ/ኪዳን ገዳ ወራሾችና በወ/ሮ ለተብርሃን በየነ ላይ ማቅረቡ በንግድ ሕግ ቁጥር 683/3/ መሠረት አግባብነት የለውም ብሎ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሥር ከሣሽ የአሁን አመልካች በዚሁ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱ ይግባኙን መርምሮ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ ለማስለወጥ ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ አመልካች በደንበኛው ላይ ለደረሰ ጉዳት የከፈለውን ገንዘብ ደንበኛውን ተክቶ የጉዳት አድራሹን ቤተሰብ በን/ሕ/ቁ/

683/3/ መጠየቅ አይችልም መባሉ፣ በተጠሪዎች መኪና የዋጋ ግምትና በተጨማሪም የተቋረጠ ገቢ አመልካች እንዲከፍል መወሰኑ ለሰበር ቀርቦ ሊጣራ እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሹ የጉዳዩ ጭብጦች፡-

አመልካች ያቀረበው ክስ ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረው በአግባቡ ነው አይደለም?

ለተጠሪ የመኪና ዋጋ ግምትና የተቋረጠ ገቢ እንዲከፈል የተወሰነው በአግባቡ ነው አይደለም? የሚሉ ናቸው፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ ያቀረበው ክስ ከላይ እንደተመለከተው ንብረትነቱ የአቶ ደረጄ ጉደታ የሆነው ተሽከርካሪ በአቶ ገ/ኪዳን ገዳ ተሽከርካሪ ግጭት ደርሶበት ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጭ በመሆኑ ከነተሳቢው ብር 783,512.50 ካሣ የተከፈለ ስለሆነና ከዚህ ገንዘብ ላይ የመኪናው ቅሪት የተሸጠበት ዋጋና እንደዚሁም የተጠሪዎች መኪና በ3ኛ ወገን ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ለተገባ የኃላፊነት ኢንሹራንስ /liability insurance/ የተከፈለው ሲቀነስ በቀሪነት ብር 396,342.00 ስለሚፈለግ ይህንኑ ገንዘብ እንዲከፍሉ ይወስንልኝ በማለት ነው፡፡ የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ መልኩ የቀረበውን ክስ ሳይቀበለው የቀረው መድን ሰጭው በን/ሕ/ቁ. 683/3/ መሠረት በመድን ገቢው ሚስትና ልጆች ላይ የመዳረግ መብት ስለሌለው ለደንበኛው የከፈለው ገንዘብ ይተካልኝ በማለት ጥያቄ ማቅረብ አይችልም በሚል ነው፡፡

የንግድ ሕግ ቁጥር 683 ስለ ኢንሹራንስ ሰጭው በምትክነት መግባት /Substitution of insurer/ የሚመለከት ሲሆን በዚሁ መሠረትም ኢንሹራንስ ሰጭው በከፈለው ካሳ መጠን ጉዳቱ እንዲደርስ ባደረጉት 3ኛ ወገኖች ላይ ክስ ለማቅረብ ኢንሹራንስ ለገባው ሰው በተከፈለው ገንዘብ



መጠን ባሉት መብቶችና ክሶች ኢንሹራንስ ሰጭው ምትክ ሆኖ እንዲገባ በዚሁ አንቀጽ በንዑስ ቁጥር /1/ ሥር ተመልክቷል፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖም ለክፋት የተደረገ ካልሆነ በስተቀር ኢንሹራንስ ሰጭው በኢንሹራንስ ገቢው ወደ ታች የሚቆጠሩ ተወላጆች ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ወኪሎች ሠራተኞች ወይም ከእርሱ ጋር ዘወትር አብረው በሚኖሩት ሰዎች ላይ ኢንሹራንስ ሰጭው የመዳረግ መብት እንደሌለው በዚሁ ድንጋጌ በንዑስ አንቀጽ /3/ ሥር ተመልክቷል፡፡ ይህም የአጠቃላይ መርሁ ልዩ ሁኔታ /Exception to the General Rule/ እንደሆነ የሚያሳይ ሲሆን ከዚህም ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው ኢንሹራንስ ሰጭው የመዳረግ መብት የሚኖረው በሕጉ ላይ የተዘረዘሩት ሰዎች የመድን ሽፋን በተሰጠው የመድን ገቢው ንብረት ላይ በክፋት ጉዳት አድርሰው በሚገኙበት ጊዜ እንደሆነ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን አመልካች የመዳረግ መብቱን መሠረት በማድረግ በክስ የጠየቀው በተጠሪዎች መኪና ላይ ለደረሰው ጉዳት የተከፈለው ካሣ እንዲተካለት ሳይሆን በተጠሪዎች መኪና ተገጭቶ ጉዳት የደረሰበትንና ካሣ የተከፈለበትን የአቶ ደረጀ ጉደታን መኪና በተመለከተ ስለሆነ ከላይ በተጠቀሰው የንግድ ሕግ ቁጥር 683/3/ መሠረትም የመዳረግ መብት  የሚኖረው ይሆናል ማለት ነው፡፡  ሆኖም ግን የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ አመልካች የመዳረግ መብት የለውም በማለት ክሱን ሳይቀበል መቅረቱ እንደዚሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንኑ ስህተት ሳያርም መቅረቱ ለድንጋጌው የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል፡፡

ወደ 2ኛው ጭብጥ ስናልፍም የመድን ሽፋን የተገባለት የተጠሪዎች መኪና ቅሪቱ ተገምቶ ብር 250 ሺህ እንደሆነ እንደዚሁም የጉዳት ካሣ ብር 92 ሺህ እንደሆነና በድምሩ ብር 342 ሺህ አመልካች ለተጠሪዎች መክፈል እንደሚገባው በሥር ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ በማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን ተጠሪዎች ባቀረቡት የተከሳሽ ከሣሽነት ክስ የዚህ ገንዘብ ግማሹ ብር 171

ሺ.ህ ለወ/ሮ ለተብርሃን እንዲከፈል መወሰኑ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩልም ተጠሪዎች እንዲከፈላቸው የጠየቁትን የተቋረጠ ገቢ በተመለከተም አመልካች የሚከራከረው ግራ ቀኞችን ባደረግነው ውል የተቋረጠ ገቢ እንደማይከፈል ተስማምተናል በማለት ሲሆን ነገር ግን አመልካች ጉዳት የደረሰበትን የተጠሪዎች መኪና ጠግኖ ለማስረከብ ስምምነቱን የገለጸ እንደመሆኑ መጠን ከውሉ አኳያ የተቋረጠ ጥቅም ለመክፈል የማይገደደው መኪናውን ለመጠገን አስፈላጊ ለሆነው ጊዜ (ማስጠገኑ ለሚወስደው ጊዜ) ብቻ እንጂ ከዚህ አልፎ መኪናው ሳይጠገን ለቀረበት ጊዜ በሙሉ ሊሆን አይችልም፡፡ በዚሁ መሠረትም መኪናውን ለመጠገን ያስፈልጋል የተባለው የ3 ወር ጊዜ በአእምሮ ግምት ተቀባይነት ያለው ነው፡፡ በዚህ ጊዜ መኪናውን አመልካች ጠግኖ ለተጠሪዎች ካላስረከበ ደግሞ ተጠግኖ ቢሆን ኖሮ ሊያስገኝ ይችል የነበረውንና ነገር ግን ሳይከፈል የቀረውን የተቋረጠ ገቢ መክፈል ይኖርበታል ማለት ነው፡፡ መጠኑን በተመለከተም መኪናው በቀን ብር 700 ገቢ ያስገባ እንደነበር ተጠሪዎች ገልጸው በዚሁ ልክ ካሣ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ ሆኖም ግን ጉዳት የደረሰበት መኪና ይህን ያሕል ገቢ ያስገባ እንደነበር በማስረጃ አላረጋገጡም፡፡ ከውልም ሆነ ከውል ውጭ ባለ ግንኙነት የጉዳት ካሣ እንዲከፈለው የሚጠይቅ ወገን የደረሰበትን ኪሣራ /Damages/ በማስረጃ ማረጋገጥ እንደሚገባው ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1790/1/ እና 2141 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

ይሁንና ጉዳት መድረሱ እስከተረጋገጠ ድረስ የነገሩን አካባቢ ሁኔታ ግምት ውስጥ በመክተት የካሣ መጠኑን ዳኞች በርትዕ መወሰን እንዲችሉ ሕጉ ሥልጣን የሰጣቸው እንደመሆኑ መጠን በተያዘውም ጉዳይ የከፍተኛው ፍ/ቤት አመልካች በክሥ የተጠቀውን የገንዘብ መጠን በበኩሉ አስልቶ እንዲከፈል ውሣኔ መስጠቱ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡



**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. አመልካች በዚህ ጉዳይ የመዳረግ መብት ስለሌለው በክስ የጠየቀው ገንዘብ ሊከፈለው አይገባም ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ ለንግድ ሕግ ቁጥር 683/3/ የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት ስለሆነ ይህንኑ ሽረን አመልካች የመዳረግ መብት አለው ብለናል፡፡

   ስለሆነም አመልካች በመዳረግ ከጠየቀው ብር 396,342 /ሶስት መቶ ዘጠና ስድስት ሺ.ህ ሶስት መቶ አርባ ሁለት/ ላይ ግማሹን ብር 198,171 /አንድ መቶ ዘጠና ስምንት ሺ.ህ አንድ መቶ ሰባ አንድ ብር/ ተጠሪ ወ/ሮ ለተብርሃን በየነ ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡
2. አመልካች በድምሩ ብር 385,200.00 /ሦስት መቶ ሠማንያ አምስት ሺ.ህ ሁለት መቶ ብር/ ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል ተብሎ የተወሰነው የካሣ መጠን በአግባቡ ስለሆነ አጽንተነዋል፡፡
3. ግራ ቀኙ አንዱ ከሌላው የሚፈልገው ገንዘብ ሲቻቻል አመልካች ብር 187,029.00 /አንድ መቶ ሰማንያ ሰባት ሺ.ህ ሀያ ዘጠኝ ብር/ ለተጠሪ መክፈል የሚገባው ስለሆነ ይህንኑ ገንዘብ እንዲከፍል ተወስኗል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ